# ለእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች

## ለረጅም ጊዜ-የሚሠራ ተለዋጭ የእርግዝና መከላከያ (LARC)

**ወሲባዊ ግንኙነት በሚያካሂዱበት እያንዳንዱ ጊዜ እነዚህን ለመጠቀም ማስታወስ አይኖርብዎም።**

| ዘዴ | ማህጸን ውስጥ የሚቀመጥ መሳሪያ (IUD) – copper IUD<br><br>Cu-IUD | ማህጸን ውስጥ የሚቀመጥ መሳሪያ (IUD) – hormonal IUD<br><br>Mirena™ | በአካል ውስጥ የሚገባ የእርግዝና መከላከያ<br><br>Implanon NXT™ |
|---|---|---|---|
| **ይህ ምንድን ነው?** | • ትንሽ ፕላስቲክና የኮፐር እርግዝና መከላከያ መሳሪያ ሲሆን በሀኪም ወይም ልዩ ስልጠና በተሰጠው አዋላጅ ነርስ በኩል በርስዎ ማህጸን ውስጥ ይቀመጣል<br>• ስፐርም ከእንቁላል ጋር ተገናኝቶ እንዳያፈራ ያግደዋል | • ትንሽ ሆርሞን-የሚያወጣ እርግዝና መከላከያ መሳሪያ ሲሆን በሀኪም ወይም ልዩ ስልጠና በተሰጠው አዋላጅ ነርስ በኩል በርስዎ ማህጸን ውስጥ ይቀመጣል።<br>• ሆርሞኖች ቀስ ብለው ስለሚወጡ ታዲያ የማህጸንዎን አቀማመጥ እንዲቀየር በማድረግ እንቁላል እንዳይገናኝ በማገድ እርግዝናን ይከላከላል | • ትንሽ ፕላስቲክ በላይኛው ክንድዎ ባለው ቆዳ ስር ላይ በሀኪም ወይም ነርስ በኩል ይቀመጣል (አስፈላጊም ከሆነ ያወጡታል)<br>• መጠኑ ትንሽ የሆነ ሆርሞንን በመልቀቅ ታዲያ በየወሩ ለርስዎ የዘር ማመንጫዎች እንቁላል ከማውጣት ያቆመዋል |
| **ለምን ያህል ጊዜ ይሠራል?** | ቢያንስ 10 ዓመታት | 5 ዓመታት | 3 ዓመታት |
| **ውጤታማነት** | 99% | 99% | 99% |

Health and Human Services
VICTORIA State Government

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |
| **ጥቅሞች** | • ሌሎች መድሃኒቶች ተጽእኖ አይፈጥሩበትም<br>• ስልጠና ባገኙ ባለሙያዎች በቀላሉ መውጣት ይችላል<br>• ከዚያም በኋላ ለማርገዝ የሚያግድዎ አይደለም<br>• አንዴ ከገባ፣ ከሌሎች ዘዴዎች ጋር ሲነጻጸር IUD አነስተኛ ክፍያ የሚያስወጣ ነው<br>• አንዴ ከወጣ በኋላ ወዲያውኑ እንቁላል ወደ ማምረት ይመለሳሉ<br>• እንደ ማኮላሸት ውጤታማ ቢሆንም ወደ ቀድሞ መመለስ ይችላል | • ምንም እንኳን ብዙ ሴቶች ሲጠቀሙ ለመጀመሪያ ጥቂት ሳምንታት መደበኛ ያልሆነ ደም መፍሰስ ቢያጋጥማቸውም፣ ብዙጊዜ የወር አበባዎን ያቀለዋል ወይም ያቆመዋል<br>• አንዴ ከገባ፣ ከሌሎች ዘዴዎች ጋር ሲነጻጸር IUD አነስተኛ ዋጋ የሚያስወጣ ነው<br>• አንዴ ከወጣ በኋላ ወዲያውኑ እንቁላል ወደ ማምረት ይመለሳሉ<br>• እንደ ማኮላሸት ቢሆንም ወደ ቀድሞ መመለስ ይችላል | • የርስዎ ወር አበባ ደም ቀላል ሲሆን ወይም ሊቆም ይችላል<br>• በቀላሉ ሊወጣ ይችላል<br>• ከዚያም በኋላ ከማርገዝ የሚያግድዎ አይሆንም |
| **ሌሎች ግምት ውስጥ የሚገቡ** | • የርስዎ ወር አበባ ከባድ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል | • የማህጸን ነቀርሳ ችግርን ይቀንሳል | • መደበኛ ያልሆነ አስቸጋሪ የመድማት ችግር ሊፈጥር ይችላል |
| **ይህ ለማን ይስማማል?** | • ለብዙዎች ሴቶች ደህንነቱ የተጠበቀ ሲሆን ምንም ልጆች ያልወለዱ ወጣት ሴቶችንም ያካትታል<br>• ጡት ለሚያጠቡ ሴቶች<br>• በሆርሞናል እርግዝና መከላከያ ዘዴ ለማይፈልጉ ሴቶች | • ለብዙዎች ሴቶች ደህንነቱ የተጠበቀ ሲሆን ምንም ልጆች ያልወለዱ ወጣት ሴቶችንም ያካትታል<br>• ጡት ለሚያጠቡ ሴቶች<br>• የማህጸን ነቀርሳ ወይም ብዙ ደም ለሚፈሳቸው ሴቶች | • ጡት የሚያጠቡ ሴቶች |

በወሲባዊ ግንኙነት ለሚተላለፍ በሽታዎች (STIs) መከላከያ ኮንዶም ብቻ ነው።

በቪክቶሪያ መንግሥት ሥልጣን ያገኘና የታተመ፣ አድራሻ 1 Treasury Place, Melbourne.
© State of Victoria, የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፣ January 2019.
በድረገጽ <http://healthtranslations.vic.gov.au/> ላይ ቀርቧል።